የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ–ጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 8
ADDIS ABABA–28th October, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፭/፲፱፻፺፮ ዓ.ም.
የኢንቨስትመንት (ማሻሻያ) አዋጅ ................. ገጽ ፪ሺ፬፻፴፪

## CONTENTS

Proclamation No. 373/2003
Investment (Amendment) Proclamation .. Page 2432

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፭/፲፱፻፺፮
### የኢንቨስትመንት አዋጅን እንደገና ለመደንገግ የወጣውን
### አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ኢንቨስትመንት የሚመራበትን ሥርዓት ግልጽና ቀልጣፋ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ ፤

ለዚህም በሥራ ላይ ያለውን የኢንቨስትመንት ሕግ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት እንደሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢንቨስትመንት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፭/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· የስያሜ ለውጥ

በአዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ መሠረት እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተብሎ ተሰይሟል ።

፫· ማሻሻያ

የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል ።

፩) የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፰) እና (፱) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፰) እና (፱) ተተክተዋል ።

"፰· "ማስፋፋት ወይም ማሻሻል" ማለት የነባር ድርጅትን የሙሉ አቅም ምርት ወይም አገልግሎት ከ፳፭ ፐርሰንት በላይ በእሴት ማሳደግ ሲሆን ይህም በዓይነት ወይም በመጠን ወይም በሁለቱም መጨመርን የሚያጠቃልል ነው ።

### PROCLAMATION NO. 375/2003
### *A PROCLAMATION TO AMEND THE INVESTMENT RE-ENACTMENT PROCLAMATION NO. 280/2002*

WHEREAS, the system of administration of investment needs to be transparent and efficient;

WHEREAS, to this end, it has become necessary to amend the existing law on investments;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Investment (Amendment) Proclamation No. 375/2003."

2. *Renaming*

The Ethiopian Investment Authority, which has been re-estabilshed under Proclamation No. 280/2002, is hereby renamed as the Ethiopian Investment Commission.

3. *Amendment*

The Investment Proclamation No. 280/2002, is hereby amended as follows:

1) Article 2 Sub-Articles (8) and (9) of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub-Articles (8) and (9).

"8. "Expansion/upgrading" means increasing in value, by more than 25%, the full production of service capacity of an existing enterprise, be it in variety, volume, or both.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

ሐ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ፣ ወይም ማኅበሩ አዲስ የሚቋቋም ከሆነ ከዚህ በተጨማሪ የማህበርተኞቹ የመታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ ወይም የሀገር ውስጥ ባለሀብትነት ሰርተፊኬት ፎቶ ኮፒ

መ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በመንግሥት የልማት ድርጅት ከሆነ ድርጅቱ የተቋቋመበት ደንብ ፎቶ ኮፒ ወይም የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ፣ እና

ሠ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በኅብረት ሥራ ማኅበር ከሆነ የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት የማመልከቻ ቅጽ እና ሠነዶች ፤

ሀ) ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ ከሆነ በሁለት ቅጂ ፣ ወይም

ለ) ለክልል የኢንቨስትመንት አካላት የሚቀርቡ ከሆነ በአንድ ቅጂ ፣ መቅረብ አለባቸው ።”

“፲፬· <u>በውጭ ባለሀብት ስለሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ</u>

ማንኛውም የውጭ ባለሀብት አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሠነዶች ጋር በሁለት ቅጂ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት ፤

ሀ) ማመልከቻው የተፈረመው በወኪል ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሠነድ ፎቶ ኮፒ ፤

ለ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በግለሰብ ከሆነ የባለሀብቱን ማንነት የሚያሳዩ የፀና ፓስፖርት ገጾች ፎቶ ኮፒ እና ሁለት የቅርብ ጊዜ ጉርድ ፎቶግራፎች፤

ሐ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው ኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ፤ ወይም ማህበሩ አዲስ የሚቋቋም ከሆነ ከዚህ በተጨማሪ የእያንዳንዱን የማህበሩን አባላት ማንነት የሚያሳይ የፀና ፓስፖርት ገጾች ፎቶ ኮፒ፤

መ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው ውጭ ሀገር በተቋቋመ የንግድ ማኅበር የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ከሆነ የማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ወይም የዚሁ ተመሳሳይ ሰነድ ፎቶ ኮፒ ፣ እና

ሠ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በአገር ውስጥና በውጭ ባለሀብት ቅንጅት ከሆነ ከላይ በፊደል ተራ “ሐ” ከተገለጹት ሰነዶች በተጨማሪ እንደ አግባቡ የአገር ውስጥ ባለሀብቱ የመታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ ወይም የአገር ውስጥ ባለሀብትነት ሰርተፊኬት ፎቶ ኮፒ ።”

“፲፭· <u>ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል ስለሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ</u>

፩) ማንኛውም ባለሀብት የማስፋፋት ወይም የማሻሻል የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሠነዶች ጋር ማቅረብ አለበት ፤

ሀ) የማመልከቻ ቅጹ የተፈረመው በወኪል ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሠነድ ፎቶ ኮፒ፤

ለ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በንግድ ማኅበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ፣ እና

ሐ) የንግድ ድርጅቱ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ ።

(c) Where the investment is to be made by a business organization, photocopies of its memorandum of association and Articles of association; or where the business organization is to be newly established, in additon, it shall submit photocopies of the shareholders' idntifty cards or photocopies of certificates evidencing there domestic investor status;

(d) Where the investment is to be made by a public enterprise, a photocopy of the Regulation under which it is established or a photocopy of its memorandum of association and Articles of association; and

(e) Where the investment is to be made by a cooperative society, a photocopy of its Articles of association.

2) The application form and documents stipulated under Sub-Article (1) of this Article shall be made:

(a) in two copies, where they are to be submitted to the Commission; or

(b) in one copy, where they are to be submitted to Regional Investment Organs''.

*''14. Application for Investment Permit by a foreign Investor*

Application for Investment Permit by a Foreign investor shall be made in a form designed for such purpose and submitted to the commission together with the following documents in two copies:

(a) where the application is signed by an agent, a photocopy of his power of attorney;

(b) where the investment is to be made by an individual person, a photocopy of the pages of a valid passport showing his identity and his recent two passport size photographs;

(c) where the investment is to be made by a business organization incorporated in Ethiopia, photocopies of its memorandum of association and Articles of association; or where it is to be newly established, in addition, it shall submit photocopies of the pages of a valid passport of each shareholder showing his identity;

(d) where the investment is to be made by a branch of a foreign business organization in Ethiopia, photocopies of its memborandum of association and Articles of association or a similar document of the parent company; and

(e) where it is a joint investment by domestic and foreign investors, in addition to the documents provided under (c) above, photocopies of identity cards or photocopies of certificates evidencing the domestic investor status of the domestic investors, as the case may be.''

*''15 Application for Investment Permit for Expansion or Upgrading*

1) An application for investment permit to expand or upgrade an existing enterprise shall be made in a form designed for such purpose and submitted together with the following documents:

a) where the application is signed by an agent, a photocompy of his power of attorney;

b) where the investment is made by a business organization, photocopies of its memorandum of association and Articles of association; and

c) photocopy of a valid business license of the existing enterprise.

፲፬) የአዋጁ አንቀጽ ፴ ተራ ቁጥር (፱) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር (፱) ተተክቷል ፡፡

"፱· ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶችን በመፍቀድ ይመዘግባል ፤"

፲፭) የአዋጁ አንቀጽ ፴፩ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፫ ተተክቷል ፡፡

"፴፫ <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

ኮሚሽኑ ፤

ሀ) በመንግሥት የሚሾም ኮሚሽነር ፤ እና

ለ) አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል ፡፡"

፲፮) የአዋጁ አንቀጽ ፴፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል ፡፡

"፪· እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አያይዞ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይኖርበታል ፤

ሀ) ማመልከቻው የተፈረመው በወኪል ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሰነድ ፎቶ ኮፒ ፤

ለ) የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ ፤

ሐ) የዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት ፎቶ ኮፒ ፤

መ) የፀና የመኖሪያ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ ፤

ሠ) የንግድ ሥራ ፈቃዱ የማኅበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ፤

ረ) አመልካቹ እንደአገር ውስጥ ባለሀብት ለሚቆጠር መደበኛ ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ጥገኛ ወይም ወራሽ ከሆነ አስጠጊው ወይም አውራሹ እንደአገር ውስጥ ባለሀብት የሚቆጠር ስለመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ሰነዶች በተጨማሪ የጥገኛው የፀና የመኖሪያ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ ፤ ወይም አመልካቹ ወራሽ ለመሆኑ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ፎቶ ኮፒ ፤

ሰ) የአመልካቹ ሦስት የቅርብ ጊዜ ጉርድ ፎቶግራፎች፡፡"

፲፯) በአዋጁ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፩ ተጨምሮ ከ፴፱–፵፪ ያሉት የአዋጁ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፵፪–፵፭ ሆነው ተስተካክለዋል ፡፡

"፵፩· <u>ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣንና ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ስለተሰጠ ውክልና</u>

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣንና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ፤

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በውክልና የተሰጣቸውን ተግባር የሚያከናውኑት በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

ለ) በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት የሰጧቸውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ ኮፒ እና አግባብ ያላቸውን ሰነዶች ፎቶ ኮፒ ለኮሚሽኑ ያስተላልፋሉ፡፡"

14) Article 30 item number (9) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new item number (9).

"9. approve and register technology transfer agreements related to investments;"

15) Article 31 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 33.

*"33. Organization of the Commission*

The Commission shall have:

(a) a Commissioner to be appointed by the Government; and

(b) the necessary staff."

16) Article 37 Sub-Article (2) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2)

"2. A foreign national permanently residing in Ethiopia to be taken for a domestic investor shall fill a form designed for such purpose and submitted together with the following documents to the commission:

(a) where the application is signed by an agent, his power of attorney;

(b) a photocopy of valid business license;

(c) a photocopy of principal registration certificate;

(d) a photocopy of valid residence permit;

(e) where the business license is that of a business organization, photocopies of its memorandum of association and Articles of association;

(f) where the applicant is dependent or heir of a person taken for a domestic investor and permantly residing in Ethiopia, in addition to the above mentioned documents pertaining to the supporting person or the deceased, a photocopy of the dependent's valid residence permit or a court decision declaring his status as an heir; and

g) the applicant recent three passport size photographs".

17) The following new Article 41 is added. Accordingly, Articles 39-42 of the Proclamation are renumbered as Articles 42-45, respectively.

"41. Power Delegated to the Ethiopian Civil Aviation Authority and the Ethiopian Electric Agency.

The Ethiopian Civil Aviation Authority and the Ethiopian Electric Agency shall:

(a) carry out functions delegated to them under Article 25 Sub–Article (2) in compliance with this Proclamation and Regulations and Directives issued thereunder.

(b) forward to the Commission photocopies of the investment permits they issued and the relevant documents".

፬· <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ፣ ፲፬ ፣ ፲፭ እና ፴፯ የተጠቀሱትን ሰነዶች ዝርዝር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ሊያሻሽል ይችላል ።

፭· <u>የተሻረ ሕግ</u>

የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፳፩/፲፱፻፹፭ በዚህ አዋጅ ተሽሯል ።

፮· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

4. *Power to Issue Regulations*

The Council of Ministers may issue Regulations to amend the list documents stipulated under Articles 13, 14, 15 and 37 of this Proclamation.

5. *Repealed Law*

Transfer of Technology Council of Ministers Regulation No. 121/1993 is hereby repealed.

6. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 28th day of October, 2003.

Done at Addis Ababa, this 28th day of October, 2003.

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA